# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ
## ፪(2)ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተስማማ

አስማምቶ አዘጋጆች

ሞላ መኮንን አበራ
ይርገዱ ተድላ በየነ

የጥራት ክትትል

ፍሬህይወት አሠፋ ከበደ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለምዓቀፍ የልማት ድርጅት /United States Agency for International Development (USAID)/ በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮና READ TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም /General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II/ ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው።

ISBN: 978-99944-2-359-0

# ማውጫ

ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች ........ v

1ኛ ሳምንት ........ 1

2ኛ ሳምንት ........ 6

3ኛ ሳምንት ........ 12

4ኛ ሳምንት ........ 18

5ኛ ሳምንት ........ 24

6ኛ ሳምንት ........ 29

7ኛ ሳምንት ........ 34

8ኛ ሳምንት ........ 38

9ኛ ሳምንት ........ 42

10ኛ ሳምንት ........ 46

11ኛ ሳምንት ........ 50

12ኛ ሳምንት ........ 54

13ኛ ሳምንት ........ 59

14ኛ ሳምንት ........ 63

15ኛ ሳምንት ........ 67

| | |
|---|---|
| 16ኛ ሳምንት | 71 |
| 17ኛ ሳምንት | 75 |
| 18ኛ ሳምንት | 79 |
| 19ኛ ሳምንት | 83 |
| 20ኛ ሳምንት | 87 |
| 21ኛ ሳምንት | 91 |
| 22ኛ ሳምንት | 95 |
| 23ኛ ሳምንት | 99 |
| 24ኛ ሳምንት | 103 |
| 25ኛ ሳምንት | 107 |
| 26ኛ ሳምንት | 112 |
| 27ኛ ሳምንት | 116 |
| 28ኛ ሳምንት | 120 |
| 29ኛ ሳምንት | 124 |
| 30ኛ ሳምንት | 128 |

# ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሕጻናትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የማዳመጥና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማበልፀግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃትምህርት አካል ነው። መጽሐፉም ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ሕጻናት ማንበብና መጻፍ እንዴት እንደሚማሩ የሚረዱ ጥናቶችንና የአማርኛ ቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት ነው።

የዚህ የአፍመፍቻ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርትና መርሃትምህርት መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው።

1. ሕጻናት እንግዳ ቃላትን ለማንበብና ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር ለመጻፍ፣ የቋንቋው ፊደላት የሚወክሏቸውን ድምፆች መማር ይጠበቅባቸዋል።

2. ሕጻናት በተቻለ መጠን በቅድሚያ ቃላትን ቀጥሎም ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ አለባቸው። እነዚህ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች በተማሯቸው ፊደላት የተመሠረቱ መሆን አለባቸው።

3. ሕጻናት በፍጥነት፣ በትክክልና ያለችግር እንዲያነቡና ራሳቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በትክክልና በግልጽ ቋንቋ ለመግለጽ እንዲችሉ የማንበብና የመጻፍ በርካታ ተከታታይ ልምምዶች ማድረግ አለባቸው፤

4. ሕጻናት አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የቃላቱንም ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን መረዳት ይችላሉ፤ ቋንቋቸውንም በንግግርና በጽሑፍ በአግባቡ ይጠቀሙበታል፤

5. ሕጻናቱ ተረቶችን/ታሪኮችንና ሌሎች ጽሑፎችን ሲያነቡ ሀሳቡን ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ማዳበር አለባቸው።

## ልጆችዎን በቤት ውስጥ ይርዱ!

ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብና መጻፍ እንዲማሩና ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ በቤት ውስጥ መርዳት ከሚችሉባቸው አጠቃላይ መንገዶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

1. ለልጅችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን ይንገሯቸው::
2. ልጅችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው::
3. ልጅችዎን እርስዎ ስላነበቡላቸው ወይም ስለነገሯቸው ተረቶች/ታሪኮች ያሏቸውን አስተያየቶች ለሌሎቻችሁ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው:: ይህም የአዳምጦ፣ የአንብቦ መረዳትና ጥሩ የመናገር ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል::
4. ለልጅችዎ ራስዎ ወይም ሌሎች ተረት/ታሪክ እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፤ ይህም ለልጆቹ የሚያነቡትን ጽሑፍ በሌላ ሰው ሲነበብ ምን እንደሚመስል የማዳመጥ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፤ በራሳቸውም ለማንበብም ፍላጎት ያሳድርባቸዋል:: ከልጆቹም ጋር ስለምታነቡት ጽሑፍ ተወያዩ::
5. በሚያውቋቸው (በተማሯቸው) ፊደላት የተመሠረቱ ቃላትን እንዲያነቡ ያድርጓቸው::
6. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ለደረጃቸው የሚመጥኑ ቀላል ጽሑፎችን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው:: ለማንበብ የሚቸገሩባቸውን ቃላትና ዓረፍተነገሮች እንዲያነቡ ያግዟቸው::
7. ልጅችዎ በራሳቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው::
8. ልጅችዎ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞቻቸው በራሳቸው ማስታወሻ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው::

## የትምህርቱ ክፍሎች (ይዘቶች)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱ ትምህርት በምልክት የተጠቆሙ ክፍሎች አሉት፡፡ ጥቂት ክፍሎች በተወሰኑ ትምህርቶች ውስጥ ብቻ የሚከሰቱ ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ክፍሎች ግን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

## የማዳመጥ ምንባብ

ይህ ክፍል የሚያተኩረው በአዳምጦ መረዳት ላይ ነው፡፡

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- በመምህራቸው የሚነበበውን ተረት/ታሪክ ወይም መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ያዳምጣሉ፤
- ርዕሱንና ሥዕሎችን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሆነ ይገምታሉ/ያስባሉ፤
- ካዳመጡት ምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በምንባቡ ላይ ይወያያሉ፡፡

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆች ስለምንባቡ የሚያስታውሱትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፤ ሥዕሎቹ ተረቶቹን/ታሪኮቹን ለማስታወስ ሊረዷቸው ይችላሉ፡፡

## አዲስ ወይም ተተኳሪ ፊደል

ይህ ክፍል በተተኳሪ ፊደላት ላይ የሚያተኩር ነው። ይህም የሚገኘው በትምህርት ዓመቱ ባሉት የመጀመሪያ አምስት ሳምንታት ውስጥ ብቻ ነው።

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ከዚህ ቀደም ያልተማሯቸውን ሞክሼና ውስብስብ ፊደላት ይማራሉ፤
- ፊደሎች በቃላት ውስጥ ያላቸውን ንበት (ምን ዓይነት ድምጽ እንዳላቸው) ይማራሉ፤
- በእያንዳንዱ ፊደል የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን ለመለየት ይችላሉ፤
- ፊደላቱን በማየት የሚወክሏቸውን ድምፆች መጥራት ይለማመዳሉ፤
- የተማሯቸውን ፊደላት ይለማመዳሉ።

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፡-

- ሕጻናቱ ቀደም ብለው የተማሯቸውን ፊደላት መመልከት ይችላሉ፤
- ሕጻናቱን ፊደሎቹ ማን ማን እንደሆኑና የሚወክሏቸውም ድምፆች የትኞቹ እንደሆኑ ይጠይቋቸው፤
- በተለያዩ ፊደሎች የሚጀምሩ ቃላትን አስበው እንዲነግሩዎ መጠየቅ ይችላሉ።



## ማጣመር/መነጠል

ይህ ክፍል ቃላትን በማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያግዛቸዋል::

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ:-

- ቃላትን “ማጣመር”:- ቃላቱ የተመሠረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሀዶች ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይሏቸዋል፤
- ቃላትን “መነጠል”:- ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላቱ ወይም ወደአነስተኛ አሀዶች ይነጣጥላሉ፤
- ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሀዶች (ቅጥያዎችን) ለይተው ያነባሉ::

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችን የቃላቱን ፊደሎች ወይም አሃዶች እንዴት እንደሚያጣምሩና እንደሚነጥሉ ይጠይቋቸው:: ለልጆቹ ይሄ ጠቃሚ ልምምድ ነው::



## ግለንባብ

ይህ ክፍል ሕጻናቱ አዳዲስ ቃላትንና ተዘውታሪ ቃላትን ማንበብ እንዲችሉ ዓረፍተነገሮችን፣ አጫጭር ተረቶችን/ታሪኮችን ወይም መረጃ ሰጪ ምንባቦችን እንዲያነቡ በማድረግ ላይ ያተኩራል:: ከዚህ በተጨማሪም በአንብቦ መረዳትም ላይ ያተኩራል::

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ግለንባቡን ያነባሉ፣
- ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣
- በግለንባቡ ላይ ይወያያሉ፣
- ስለምንባቡ በደረጃቸው ይጽፋሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፡-

- የዕለቱን ግለንባብ ይመልከቱና ልጆቹ እንዲያነቡ ይጠይቋቸው፣
- የቀደሙ ግለንባቦችን ይመልከቱና እንዲያነቡልዎ ይጠይቋቸው፣
- ልጆችዎ በግለንባቡ ውስጥ ለማንበብ የሚቸገሩባቸው ማናቸውም ቃላት ካሉ ቃላቱን እንዲለዩዋቸውና እንዲያነቧቸው ያበረታቷቸው፣
- ልጆችዎ ግለንባቡን መውደድ አለመውዳቸውንና ለምን እንደወደዱት ወይም እንዳልወደዱት ይጠይቋቸው።

## ቃላት

ይህ ክፍል አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም ላይ ያተኩራል።

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ:-

- ከመምህራቸውና ከሚያዳምጡት ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ፤
- አዳዲስ ቃላትን ከሥዕሎች ወይም ፍቻቸው ጋር ያዛምዳሉ፤
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ፤
- ቃላቱን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም ይለማመዳሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ ቀደም ሲል በተማሯቸው ትምህርቶች ውስጥ ያሉ ሥዕሎችን ተመልክተው በሥዕሎቹ የተወከሉትን ቃላት እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።
- ልጆችዎ ስለተማሯቸው ቃላት እንዲነግሩዎ ይጠይቋቸው።

## መጻፍ

ይህ ክፍል ፊደላትንና ቃላትን በመጻፍ፣ እንዲሁም ሀሳባቸውን በሥዕልና/ወይም በቃላት በመግለጽ ላይ ያተኩራል።

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ:-

- ፊደላትን መጻፍ ይለማመዳሉ፤
- በተማሯቸው ፊደላት ቃላትን ይጽፋሉ፤
- ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር መጻፍ ይለማመዳሉ፤
- አጫጭር የቃል ጽሕፈትና የፊደል አሰዳደር ሙከራዎች ይወስዳሉ፤
- ሃሳባቸውንና ግንዛቤያቸውን ለሌሎች ለማካፈል ዓረፍተነገሮችን ይጽፋሉ፡፡

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣


- ልጆችዎ የእጅ ጽሕፈታቸውን እንዲያሻሽሉ ፊደላትንና ቃላትን እንዲገለብጡ ይጠይቋቸው፡፡
- ቃላትን በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት በጽሑፍ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡
- ልጆችዎ በሚሳሳቱበት ጊዜ ያበረታቷቸው፤
- ልጆችዎ አጫጭር ዓረፍተነገሮች እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ይህም ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች አጫጭር ማስታወሻዎች እንዲጽፉ በማለማመድ ሊተገበር ይችላል፡፡

# 1ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የልብስ ዓይነቶችና ቀለማቸው**



### ቃላት

**በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።**

ምሳሌ:- ኮት → መምህሩ ኮት ለበሱ።

1. ቀሚስ  2. ጋቢ  3. ቁምጣ  4. ሸሚዝ

### ሞክሼ ፊደላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ | ሐ | ኀ | ኸ |

**ፊደላቱን ፃፉና አንብቡ።**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |

## ማጣመር

አጣምራችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

| | | |
|---|---|---|
| ሀ-ብ-ት | ሐ-ብ-ት | ኀ-ብ-ት |
| ህ-ል-ም | ሕ-ል-ም | ኅ-ል-ም |

## ግለንባብ

### የአበባ አዳዲስ ልብሶች



አበባ ልብስዋ አልቆባታል:: ከአባትዋ ጋር ወደገበያ ሄደች:: ወደህፃናት ልብስ ሱቅ ገቡ:: ከጥጥ የተሰሩ ልብሶችን አዩ:: አባትዋ ቀይ ቀሚስ፣ ነጭ ሹራብና ቢጫ ካልሲ ገዙላት:: ስለዚህ አበባ በጣም ተደሰተች::

## 2ኛ ቀን

## ሞክሼ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ሠ | ሰ |

ፊደላቱን ፃፉና አንብቡ::

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |

## መነጠል

ነጥላችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

ምሳሌ:- ሠርግ → ሠ ር ግ

1. ሥጦታ
2. ሰማይ
3. ስቃይ

## አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. በሱቅ ውስጥ ምን ምን ዓይነት ልብሶች ይሸጣሉ?
2. አበባ ምን ምን ዓይነት ልብሶች ተገዙላት?
3. አበባ የተደሰተችው ለምንድን ነው?

## ቃላት

**ቃላቱን በብዙ ቁጥር ፃፉ፡፡**

ምሳሌ:- ሰው → ሰዎች

1. ልብስ 2. ቀሚስ 3. ሹራብ 4. መቀነት

## መፃፍ

**በምሳሌው መሰረት ቃላቱን መድቡ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኮት | ሸሚዝ | ጉርድ ቀሚስ | የውስጥ ሱሪ |
| ጋቢ | ኩታ | የአንገት ልብስ | የአበሻ ቀሚስ |

| | ባህላዊ ልብሶች | ዘመናዊ ልብሶች |
|---|---|---|
| ምሳሌ→ | ጋቢ | ኮት |

## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

**የልብስ ዓይነቶችና ቀለማቸው**



## ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ቀይ → <u>የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀይ ቀለም አለው</u>።

1. አረንጓዴ  2. ቢጫ  3. ጥቁር  4. ነጭ

## ሞክሼ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ጸ | ፀ |

ፊደላቱን ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ጸ ጹ ጺ ጻ ጼ ጽ ጾ    ፀ ፁ ፂ ፃ ፄ ፅ ፆ

## ማጣመርና መነጠል

አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ጸ - ሀ - ይ    ፀ - ሀ - ይ


ነጥላችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ጾም    ፆም

## ግለንባብ

### አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላት

አቅጣጫ ለማመልከት አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላትን እንጠቀማለን። እነሱም ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ ቀኝ፣ ግራ፣ ራስጌና ግርጌ የተባሉት ቃሎችም አቅጣጫ ጠቋሚዎች ናቸው።



## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በትክክል በጽሁፍ መልሱ።

1. ጓደኞቻችሁ በየት በኩል ተቀምጠዋል?
2. መምህራችሁ ከእናንተ በየት በኩል ይገኛሉ?
3. ጥቁር ሰሌዳው ከእናንተ በየት በኩል ይገኛል?
4. ቢሮው ከክፍላችሁ በየት በኩል ይገኛል?
5. አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላት ምን ምን ናቸው?

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ሰሜን → ቤቴ ከትምህርትቤቱ በስተሰሜን ይገኛል።

ደቡብ ምስራቅ ምዕራብ

### መፃፍ

የጥያቄዎቹን መልሶች በፅሁፍ ግለፁ።

1. ምን ምን ዓይነት ልብሶችን ለብሳችኋል?
2. የልብሶቻችሁን ቀለሞች ፃፉ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**ቀኍብሽ በገና በዓል**

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ::

ምሳሌ:- ውበት → ውበትን መጠበቅ ቆንጆ ያደርጋል::

1. ኩታ 2. የገና በዓል 3. እሩር 4. የባህል ልብስ

### ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ኗ | ሟ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ::

| | |
|---|---|
| ኗ | ሟ |

### ማጣመር

አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ::

ምሳሌ:- ሟ ሟ → ሟሟ

1. ባ ኗ 2. ላ ሟ

የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ቃላት መስርቱ::


ምሳሌ:- በሰለ:- ሰለበ

1. ቀመረ 2. ከመረ 3. በደለ

## ግለንባብ

### የልብስ ጥቅም

ልብሶች ብዙ ጥቅም አላቸው:: ብርድን ይከላከላሉ፤ ውበትና ድምቀትን ይሰጣሉ:: ሰዎች እንደየሙያቸው የተለያዩ የደንብ ልብሶችን ይለብሳሉ:: ለምሳሌ ተማሪዎች፣ መምህሮች፣ ወታደሮች፣ ሐኪሞች የየራሳቸው የደንብ ልብሶች አሏቸው::



## 2ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ሏ | ሿ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ::

| | |
|---|---|
| ሏ | ሿ |

## ማጣመር

አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ::

ምሳሌ:- ል ብ ሏ → ልብሏ

1. እ ሏ

2. ሻ ሿ


## አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ልብሶች ምን ምን ጥቅሞችን ይሰጣሉ?
2. የደንብ ልብስ የሚለብሱ እነማን ናቸው?

## ቃላት

በሳጥኖቹ ውስጥ ተስማሚ ቃላትን ፃፉ፡፡




## መፃፍ

ዓረፍተነገር ፃፉ፡፡

ምሳሌ፦ ግርጌ → ጋቢዬን ከአልጋዬ ግርጌ አስቀምጣለሁ፡፡

1. ራስጌ    2. ፊትለፊት    3. በስተኋላ


## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ቀኑብሽ በገና በዓል

## ቃላት

ቃላቱን ከሥዕላዊ መግለጫዎች ጋር አዛምዱ::

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| ሐ | 1. ቀሚስ | ሀ. |  |
| | 2. ሹራብ | ለ. |  |
| | 3. ጋቢ | ሐ. |  |
| | 4. ኮት | መ. |  |
| | 5. ሸሚዝ | ሠ. |  |

## ውስብስብ ፊደላት

| | | |
|---|---|---|
| ቧ | ቷ | ቿ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ::

| | | |
|---|---|---|
| ቧ | ቷ | ቿ |

## ማጣመር

አጣምራችሁ አንብቡ::

1. ሹ ራ ቧ   2. ባ ቷ   3. አ ማ ቿ

## ግለንባብ

### የሀብታሙ መኝታቤት



ሀብታሙ ሁልጊዜ ከትምህርትቤት ሲመለስ ለመጫወት ይቸኩላል:: የደንብ ልብሱንና ቦርሳውን ባገኘበት ቦታ ይጥላል:: አንድ ቀን እናቱ ወደመኝታቤቱ ገቡ:: መኝታቤቱ ተዝረክርኮ አዩ:: በጣም ተናደዱ:: ሀብታሙን ጠሩትና "ጥፋትህን አውቀሃል?" ሲሉ ጠየቁት:: "አዎ እማዬ! አሁን አስተካክላለሁ" አለ:: ወዲያው የደንብ ልብሱን ከአልጋው ራስጌ ባለው ቁምሳጥን ውስጥ አጣጥፎ ከተተ:: ቦርሳውን ከፊት ለፊት ባለው መደርደሪያ ላይ አስቀመጠ:: ጫማውን ከአልጋው ሥር አኖረ:: እናቱ ተመልሰው መጡ:: ሳቅ አሉና አቅፈው ሳሙት::

## 4ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ኗ | ኟ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ::

| | |
|---|---|
| ኗ | ኟ |

## መነጠል

ፊደሎቹን ነጥላችሁ ፃፉና አንብቡ::

ምሳሌ፦ ኗሪ → ኗ ሪ

1. ምኗ 2. ጎኗ 3. ሞኟ 4. ቀኟ 5. ትንኟ

## አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ::**

1. የሀብታሙ እናት የተናደዱት ለምንድን ነው?
2. ሀብታሙ በሠራው ጥፋት ተፀፅቶ ምን አደረገ?

## ቃላት

**ፊደላቱን መድረሻ በማድረግ ቃላትን መሥርቱ::**

ምሳሌ፦ ቷ → ጡቷ፣ ባቷ፣ ላቷ፣ ራቷ፣ ፊቷ

1. ቧ
2. ቿ

## መፃፍ

**በዓውዳመት (በበዓል) ቀን ምን ምን ዓይነት ልብሶችን ትለብሳላችሁ? በጽሑፍ ግለፁ::**

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**ተሸላሚው ከድር**

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ንፁህ → ከድር ንፁህ ልብስ ለብሷል።

1. ማጠብ 2. ማጠፍ 3. ማስቀመጥ

### ውስብስብ ፊደላት

| ዟ | ኟ |
|---|---|

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

| ዟ | ኟ |
|---|---|

### ማጣመር

ሀ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላት መስርቱ።

አ ዟ ሪ　　　　አ ዛ ኟ

ለ. የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ቃላት መስርቱ።


ምሳሌ፦ ቀና → ናቀ

1. ላጠ 2. ላገ 3. ሠራ 4. ላብ 5. ረዳ 6. ገዛ

# ግለንባብ

## የልብስ ንፅህና

የግል ንፅህናን ለመጠበቅ ልብስን ማጠብ አስፈላጊ ነው፡፡ ልብስ በጠጣር፣ በፈሳሽና በዱቄት ሳሙና ይታጠባል፡፡ ልብስ ከታጠበ በኋላ በፀሃይ ወይም በነፋስ ይደርቃል፡፡ የደረቀውን ልብስ አጣጥፎ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡ ደርቀው የታጠፉ ልብሶች በልብስ ቁምሳጥን፣ በሳጥን፣ በሻንጣ፣ ወይም በሌሎች ማስቀመጫዎች ይቀመጣሉ፡፡



## 2ኛ ቀን

# ውስብስብ ፊደላት

| ዷ | ጇ |
|---|---|

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ፡፡

| ዷ | ጇ |
|---|---|

# ማጣመር

ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላትን መስርቱ፡፡

ድ ዷ          ደ ጇ

# አንብቦ መረዳት


ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ በትክክል መልሱ፡፡

1. ልብሳችሁ ሲቆሸሽ ምን ታደርጋላችሁ?
2. የግል ንፅህናችሁን ባትጠብቁ ምን ጉዳት ይደርስባችኋል?

## ቃላት

ቃላቱን ከስዕሎቹ ጋር አዛምዱ።

____ ማስቀመጥ ____ ማድረቅ ____ ማጠብ ____ ማጠፍ

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| 1. | 2. | 3. | 4. |



## መፃፍ

በእረፍት ቀናችሁ ወላጆቻችሁን ምን ዓይነት ሥራዎችን በመሥራት ታግዛላችሁ? በዝርዝር ፃፉ።

# 3ኛ ቀን


## ማዳመጥ

### ተሸላሚው ከድር

| | |
|---|---|
|  |  |
|  |  |

## ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎች የድርጊት ቅደምተከተል ማሳያ ቃላትን በሳጥኖች ውስጥ ሙሉ::




## ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ሯ | ፏ |

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

| | |
|---|---|
| ሯ | ፏ |

## ማጣመር

ሀ. ፊደላቱን በማጣመር ቃላትን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ::

1. ፏ ፏ ቴ

2. አ ገ ሯ

ለ. የፊደላትን ቦታ በማቀያየር ሌሎች ቃላትን መስርቱ::

ምሳሌ:- ቃጣ → ጣቃ

1. ማገ 2. ደራ 3. ቀራ 4. ራበ 5. ጠና

## ግለንባብ

### የዝናሽ ልብስ



ዝናሽ የአዲስ አበባ ከተማ ፏሪና ሠራተኛ ናት። ትዳር የላትም። ልብሷን የምታሳጥበው በልብስ አጣቢዎች ነው። አበበ በዚህ ሙያ ከሚተዳደሩ ሰዎች አንዱ ነው። ዘወትር የዝናሽን ልብስ አጥቦ፣ አድርቆ፣ ተኩሦና አጣጥፎ ያስረክባታል። በዚህም ተግባሩ ሁልጊዜ ታመሰግነዋለች።

## 4ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| ጧ | ጯ |
|---|---|

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

| ጧ | ጯ |
|---|---|

## ማጣመር

ፊደላቱን በማጣመር ቃላትን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

1. ጧ ፍ
2. ጯ ሂ

## አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ዝናሽ የምትኖረው የት ነው?
2. የዝናሽን ልብስ ያጠበው ማን ነው?
3. ዝናሽ ልብሷን የምታሳጥበው ለምን ይመስላችኋል?

## ቃላት

| በ | መ | ጠ | ረ | ሰ | ወ |
|---|---|---|---|---|---|

እነዚህን ፊደላት በተገቢው ቦታ በመጠቀም ቃላት መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ቀ በ ረ → ቀበረ    ፈ ረ ሰ → ፈረሰ

ቀ - ረ    ቀ - ረ    ቀ - ረ    ቀ - ረ

## መፃፍ

በሳምንቱ ቀኖች ውስጥ የሰራችኋቸውን ሥራዎች ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሰኞ ወደትምህርት ቤት መጣሁ፡፡

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

ትንሹ ሰይድ

### ቃላት

በክፍት ቦታዎች ተገቢ ቀናትን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- አንደኛው ቀን <u>ሰኞ</u> ነው፡፡

ሁለተኛው ቀን ________________ ነው፡፡

ሶስተኛው ቀን ________________ ነው፡፡

ሰባተኛው ቀን ________________ ነው፡፡

### ውስብስብ ፊደላት

| | | |
|---|---|---|
| ቄ | ቊ | ቍ |

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቄ | ቊ | ቍ |

### መነጠል

ፊደላቱን ነጥላችሁ ፃፉና እያንዳንዱን ፊደል ድምፅ በማሰማት አንብቡ፡፡

ምሳሌ፡- ቊልፍ → ቊ ል ፍ

ቊርጥ ቄሰፊ

## ግለንባብ

### ዙሪያ ክብ ጨዋታ



በቀለች፣ ከበደ፣ ሰሚራና አሊ የአንድ ሰፈር ልጆች ናቸው። ዛሬ እለቱ እሁድ ነው። ከነበቀለች ሰፈር ትንሽ ሜዳ አለ። ሜዳው ላይ ክብ ሠርተው ይጫወታሉ። የመሃል ዳኛው አሊ ነው። አሊ "ሰኞ" ሲል ሁሉም ይቆማሉ፤ "ማክሰኞ" ሲል ሁሉም ይቀመጣሉ። "ረቡዕ" ሲል ሁሉም ይተቃቀፋሉ። ከነዚህ ውጭ ሌሎቹ ቀናት ሲጠሩ ይንቀሳቀሳሉ። ጨዋታው ተጀመረ። አሊ "ቅዳሜ" አለ። ከበቀለች በስተቀር ሌሎቹ ተቃቀፉ። በቀለች የጨዋታው አሸናፊ ሆነች።

## 2ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| ቋ | ቌ |
|---|---|

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

| ቋ | ቌ |
|---|---|

## መነጠል

ፊደላቱን ነጥላችሁ ፃፉና እያንዳንዱን ፊደል ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ምሳሌ፦ ቋመጠ → ቋ መ ጠ

ቋንቋ ቋንጣ ቋራ

## አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. የእነበቀለች የጨዋታ ህግ ምንድን ነበር?
2. የጨዋታው የመሃል ዳኛ ማን ነበር?
3. ቅዳሜና እሁድ ምን ዓይነት ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ?

## ቃላት

**ቃላትን በምሳሌው መሠረት መስርቱ።**

ምሳሌ፦ ቆመ ብሎ ይቆማል ካለ፣

1. በላ ብሎ → _____ ይላል።
2. ሮጠ ብሎ → _____ ይላል።
3. ጠለፈ ብሎ → _____ ይላል።
4. አጠበ ብሎ → _____ ይላል።

## መፃፍ

**መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገር በማዳመጥ በትክክል ፃፉ።**

## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ትንሹ ሰይድ



## ቃላት

**በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።**

1. ቅዳሜ
2. እሁድ
3. ቀን
4. ሳምንት

## ውስብስብ ፊደላት

| ጐ | ጒ | ጕ |
|---|---|---|

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

| ጐ | ጒ | ጕ |
|---|---|---|

## ማጣመርና መነጠል

ሀ. ፊደላትን አጣምራችሁ ቃላት አንብቡ።

ጕ ለ መ ና　　　　ጕ ል ቆ

ለ. በነጠላ ቁጥር ፃፉ።


ምሳሌ፦ ቀኖች → ቀን

1. ሳምንቶች　2. ሰዓቶች　3. ወሮች　4. እለቶች

## ግለንባብ

### የሳምንቱ ቀኖች

አንድ ሳምንት ሰባት ቀኖች አሉት። እነሱም ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ሐሙስ፣ አርብ፣ ቅዳሜና እሁድ ናቸው። ሰኞ የመጀመሪያ ዕለት ሲሆን፣ እሁድ ደግሞ የመጨረሻ ዕለት ነው። ለመንግስት ሠራተኞች ከሰኞ እስከአርብ የሥራ ቀኖች ናቸው።



# 4ኛ ቀን

## ውስብስብ ፊደላት

| | |
|---|---|
| ኋ | ኌ |

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

| | |
|---|---|
| ኋ | ኌ |

## ማጣመር

ፊደላትን አጣምራችሁ ቃላት አንብቡ።

ት ኋ ን        በ ኋ ላ

## አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የሥራ ቀናት የሚባሉት ማን ማን ናቸው?
2. የእረፍት ቀናትስ ማንና ማን ናቸው?
3. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርታችሁን መቼ መቼ ታጠናላችሁ?

## ቃላት

ቃላቱን በማቃረን አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ቀን | ሀ. ሞቃት |
| 2. ቅርብ | ለ. ብዙ |
| 3. ነጠላ | ሐ. ሩቅ |
| 4. ቀዝቃዛ | መ. ሌሊት |

## መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ባለፈው ሳምንት የሠራችሁትን ፃፉ::

ምሳሌ፦ ቅዳሜ ልብሴን አጠብኩ::

ሀ. እሁድ ለ. ሰኞ ሐ. ማክሰኞ